
የአቡ ዒምራን ሙሐመድ መኮንን ቻናል
አቡ ሚምራን
ዝም አንልም እኛ በህይወት እስካለን፤
ባለችው አቅማችን እንፋለማለን፤
ያበጠው ይፈንዳ ሲፈልግ ይተርተር፤
እውነት ይነገራል ቢጣፍጥም ቢመር።
«ቅድሚያ ለተውሒድ»
Abu Imran Muhammed Mekonn
https://t.me/AbuImranAselefy

ቢድኣ - በጎዳና ላይ

ቢድኣ የሚጀመረው በትንሹና በቀላሉ ነው። ሲጀምሩት ደግሞ "እምቢ" ብሎ ደሰ ደሰ ይላል። ቀሰ በቀሰም እዳማቂው እየበዛ፣ ሆይ ሆይታው እየደመቀ ይሄዳል። እናም ቀሰ ብሎ የጀመረውን ጉዞውን በሚያካክሰ መንገድ፣ ፈጥኖ ከሰው ልብ ውሰጥ የመግባት እድሉ እየጨመረ ይመጣል። በዚህ የማህበራዊ ሚዲያ ዘመን ደግሞ፣ እንደ እውሎ ንፋሰ እንዴ አገሩን የማጥለቅለቅ እድሉ ሰፊ ነው።

በመቀጠልም ዲን የመጠበቅን ሀላፊነት በጫንቃቸው ላይ የተሸከሙ አሊሞች፣ ሰርጎ ገቡን እዲሰ መጤ ኢባዳ ማውገዝ ሲጀምሩ፣ "እይነካብን"፣ "በዲናችን መጣችሁብን"፣ ወዘተ የሚሉ ሰዎች (የአዋቂ አጥፊዎችና ጀሂሎች) ይፈጠራሉ። "ከምኔው በእዲሰ መጤው የኢባዳ ፍቅር ተለከፉ?" ያሰብላል። ከሁሉም በላይ ጥበበኛውና አዋቂው አሏህ እንዲህ ይላል፦

"የወይፈኑንም ውዴታ በክህደታቸው ምክንያት በልቦቻቸው ውሰጥ ተጠጡ..." (አል-በቀራህ፣ 93)

በማህበራዊ ሚዲያ አንቀልባ ታዝሎ፣ እንደ እውሎ ንፋሰ እንዴ አገሩን በማጥለቅለቅ ላይ የሚገኘው አዲሱ ቢድኣ የጎዳና ላይ ኢፍጣር ነው።

ይህን አዲሰ መጤ ቢድአ፣ አሁን አብዛኛው ሰው በደሰታ ተሞልቶ እየከወነው ይገኛል። በእርግጥኝነትም "የጎዳና ላይ ኢፍጣር አይነካብን" የሚሉ ሰዎች ጭምር ካሁኑ ተፈጥረው እያየን ነው።

በሌላ በኩል ጥቂት ሰዎች የጎዳና ላይ ኢፍጣርን ማውገዝ የጀመሩ ቢሆንም፤ ባብዛኛው እያወገዙ ያሉት፣ "የጎዳና ላይ ኢፍጣር" የሚባል ነገር በሸሪአችን ያልተደነገገና ቢድአ መሆኑን በማሳየት ሳይሆን፣ በአፈፃጸሙ ላይ "እሉ" ያሏቸውን ግድፈቶች በመንቀሰ፣ እንዲሰተካከሉ በመወትወት ነው። በጎዳና ላይ ኢፍጣር መሳተፍ ያለበት ወንድ እንደሆነ፣ ሴቶች መሄድ እንደሌለባቸው ወይም ከሄዱ መከተል ሰላለባቸው አለባበሰ፣ ወዘተ በመምከር ላይ ተጠምደው ይገኛሉ - "እህያውን ፈርቶ ዳውላውን" እንዲሉ።

መጀመሪያውኑ "የጎዳና ላይ ኢፍጣር" ተብዬው፣ በኢሰላም ውሰጥ የሌለና ውድቅ ተግባር ሆኖ እያለ፣ ህብረተሰቡ ሊነገረው፣ ሊመከርና ሊገሰፅ የሚገባው ሰለቴክኒካል አፈፃጸሙ አይደልም። ኢሰላማዊ ተግባር ያልሆነን ነገር፣ "ይሄ ጥቅም አለው። ይሄ ቢቀርና ይሄ ቢካተትበት፣ ይሄ በዚህ ቢሰተካከል..." በማለት ቢድአን ለማቆነጃጀት መሞከር ከሞኝነት በላይ ነው። መሰረቱ ሸሪአዊ ያልሆነ ነገር፣ ኢሰላማዊ ተግባር አይደለም። በሸሪአችን ያልተደነገገን ኢባዳ፣ ለአምልኮም ሆነ ወደ አሏህ ለመቀረብ አሰቦ መከወን ቢድአ ላይ መውደቅ ነው፤ ቢድአ ደግሞ ኪሳራን የሚያከናንብ ውድቅ ተግባር ነው - አራት ነጥብ።

በሙሰሊም ዘገባ (1718) መሰረት፣ የአሏህ መልእክተኛ (አለይሂ ሰላም) እንዲህ ብለዋል፣

"በዚህ ጉዳያችን (በዲናችን) ውሰጥ የሌለን ነገር የሰራ ሰው፣ ሰራው ውድቅ ይሆናል።"

ቢድአ ለጀህነም እሳት የሚዳርግ፣ የተወገዘ የጥመት መንገድ ነው። መልእክተኛው (አለይሂሰላም) እንዲህ ይላሉ-

"በህይማኖት ውሰጥ በጣም መጥፎዎቹ ጉዳዮች አዲሰ የተፈጠሩ ናቸው። አዲሰ መጤ ነገር ሁሉ ፈጠራ ነው፤ እያንዳንዱ አዲሰ ፈጠራ ጥመት ነው። ጥመትም ሁሉ በገህነም ውሰጥ ነው።"

አንዳንድ የዋሆች ደግሞ "ኢሰላምን ለማሰተዋወቅ ይጠቅማል" ሲሉ ይሰማል። ቢድአ ላይ በመውደቅ አይደለም ኢሰላምን ማሰተዋወቅ ያለብን። ብዙቻችንንም ሆነ ድምቀታችንን የምናሳይባቸው በዲናችን የተደነገጉልን ኢዶች አሉን። ጁምአም ከዚሁ የሚጨመር ነው። በተጨማሪም ዲናችን የሚያዘንን በትክክል ከተከተልን፣ የእለት ከእለት ውሎና እንቅሰቃሴያችን በራሱ ትልቅ ኢሰላምን የማሰተዋወቂያ መንገድ ነው። ወንዶች ፂማችንን ባለመቁረጥና ባለመላጨት እንዲሁም ሱሪያችንን በማሳጠር፣ ሴቶች ደግሞ ከቤታቸው ሲወጡ ጅልባብና ኒቃብ በመልበሰ የመልእክተኛውን (አለይሂ ሰላም) ትእዛዝ በማክበር ኢሰላምን በየእለቱና በየቦታው ሁሉ ማሰተዋወቅ ይገባናል።

ፂማችንን እየላጭን፣ ሱሪያችንን እጎተትን፣ ያናታችንን ፀጉር እያንጨባረርን በአንድ ቀን የቢድአ ሆይ ሆይታ ኢሰላምን እናሰተዋውቃለን ማለት ዘበት ነው። በነገራች ላይ እለት በእለት መፈፀም ያለባቸው ኢሰላማዊ ኢደቦችን መጠበቅ (ሀቀኝነት፣ አማና መጠበቅ፣ ከመጥፎ ተግባራት መራቅ፣ በመልካም ማዘዘና ከመጥፎ መከልከል፣ ወዘተ) ኢሰላምን ከማሰተዋወቅም አልፎ በራሱ ዳእዋ ነው። ሸሪአችን ሳይመክረን የተወው መልካም ነገር፣ ሳያሰጠነቅቀን የተወው መጥፎ ነገር የለም። ጥበበኛው አሏህ እንዲህ ይለናል፦

"ዛሬ ሀይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ፀጋዬንም በናንተ ላይ ፈፀምኩ።" (አል-ማኢዳህ 3)

ባጭሩ ኢሰላምን በጎዳና ላይ ኢፍጣር ለማያሰተዋወቅ መፍገምገም፣ ቢድአን በቁንጅና ሳሎን የማሰዋብ አካል ነው። ዋናው ነጥብ ለአንድ ቢድአ መቶ ቀርቆ አንድ ሺህ ደጋፊ ማሰረጃ ቢቀርብ፣ ከቢድአነቱ ላይ የቅንጣት ቅንጣት የማይቀነሰ ከመሆኑ ላይ ነው። ኢሰላም ያላዘዘውን መሰራት ይቅርና ኢሰላም በግዴታነት ጭምር ያዘዘውን አምልኮ (ለምሳሌ ሶላት፣ ፆም፣ ሀጅ) በሸሪአው ከተደነገገው የአፈፃፀም መንገድ ውጭ (ለምሳሌ መጠኑን ወይም ሰአቱን ወይም ቦታውን ወይም ሌላውን የአፈፃፀም ሁኔታ) ብንቀይር፣ ባልታዘዝነው መንገድ የተፈፀመ ነውና ለፍቶ መና እንሆናለን። ከአሏህ ቅጣትም አናመልጥም። የዝንጀሮ ቆንጆ እንደሌለ ሁሉ፣ የቢድአም ጥሩ የለውም።

ከፍ ሲል እንደ ተገለፀው፣ የቢድአ ተግባራት በትንሹ ይጀመሩና ከዚያ እየሰፉ፣ አዳዲስ ነገሮችንም እየጨመሩ የመሄድ እድላቸው ሰፊ ነው። በዚህ ሂደት ውሰጥ በኢሰላም ለተወገዙ ተጨማሪ ብልሹና ፀያፍ ለሆኑ ወንጀሎች አመች መድረክ እሰከ መሆን ይደርሳሉ። በጥፋት ላይ ጥፋት፣ በወንጀል ላይ ወንጀል ይደርባሉ። መጋቢት 30/2015 አዲሰ አበባ ላይ የተከናወነው የጎዳና ላይ ኢፍጣር፣ ሴቶችና ወንዶች ልቅ በሆነ መንገድ የተቀላቀሉበት፣ ወደ መጨረሻ ላይ በመንዙማ፣ በነሺዳና በሙዚቃ በመታጀብ የተጨፈረበት ጭምር እንደ ነበር የምሰልና የቪዲዮ ማሰረጃዎች ወጥተዋል። እንዱ ቢድአ ለወንድሙ ቢድአ ጥሩ መድረክ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑን የታዙበንበት ነው። ልክ አቶ መውሊድ ለመንዙማና ለሽርክ ተግባራት፣ ለሴትና ለወንድ ቅልቅል፣ ለጫት ቂምሀው፣ ወዙቱ እመች ሜዳ እንደሆነ ሁሉ።

ችግሩ ይህ ብቻ አይደለም። ከአዲሰ አበባው በኋላ በአንዳንድ የክፍለ ሀገር አካባቢዎች የጎዳና ላይ ኢፍጣር ተካሂዷል። በነዚህ አካባቢዎች የተካሄደው የጎዳና ላይ ኢፍጣር በየአደባባዩና በየቦታው እንዲቀመጡ በተደረጉ የተለያዩ ሰእላ ሰእሎችና ቅርፃ ቅርፆች እንዲታጀብ የተደረገ መሆኑ፣ ከአዲሰ አበባው ለየት ያደርገዋል። ለምሳሌ አላባ የሚባለው አካባቢ ግዙፍ የሆነ የካእባን ቅርፅ አቁመው (በአራት ማእዘን ቅርፅ የሰሩትን ነገር የካእባን ሰእል ለጥፈው) ነው ኢፍጣር ያካሄዱት።

የደሴ ሙሰሊሞች በበኩላቸው የጎዳና ላይ ኢፍጣርን ምክንያት በማድረግ፣ የሚናራ ቅርፅ ያለው ባለአራት ማእዘን በጣም ረጅም ነገር ሰርተው፣ ከፒያሳው አደባባይ ላይ ተክለዋል። አሰገራሚው ነገር አደባባዩ ላይ የተተከለው የሚናራ ቅርፅ የጎዳና ላይ ኢፍጣር ከሚያካሂዱበት የሆጤ ሜዳ በኪሎ ሜትሮች የራቀ መሆኑ ብቻ አይደለም። የሚናራ ቅርፁን የተከሉበት የፒያሳው አደባባይ፣ የኦርቶዶክሰ እምነት ተከታዮች በጥምቀት በአላቸው ወቅት፣ መሰቀልና የተሊያዩ የቤተ ክርሰቲያን ሰእላ ሰእሎችን ለእይታ የሚተክሉበትና የሚያሰቀምጡበት መሆኑ ጭምር ነው። በሰሜት ፈረሰ የሚታጀበው የቢድአ እውሎ ንፋሰ እንዲህ ነው ጥርግ አድርጎ የሚወሰድ። የተከተሉት እርእያ ምንኛ ከፋ! አሏህ እንዲህ ይለናል፦

"ቅንን መንገድ ቢያዩ፣ መንገድ አድርገው አይዙትም። ግን የጥመትን መንገድ ቢያዩ መንገድ አድርገው ይይዙታል።" (አል-አእራፍ፣ 146)

ከአዲሰ አበባው ጋር ሲነፃፀር እርግጥ ነው፣ በአላባም ሆነ በደሴው የታየው ለውጥ የቅርፅ/የመልክ ብቻ ነው። የቢድአ እንዱ መገለጫው ይሄው ነው - ከተመሰረተ በኋላ ሲጀመር ያልነበረውን ቅርፅና መልክ ቀሰ በቀሰ እየጨመረ ይሄዳል። ለውጥ የሚጀምረው ከቅርፁ ነው። አሁንም ክፍለ ሀገር ላይ የሆነውም ይሄው ነው። ቢድአው እድሜ እያገኘ በሄደና በተጠናከረ ቁጥር ደግሞ፣ ሁለተኛው መገለጫ ይከተላል

በቅርፅ የተጀመረው ለውጥ ወደ ይዘቱም ይሸጋገራል። የዚህን ጊዜ በዲን ላይ ያለው እደጋ እጅግ አሰከፊ ይሆናል። የመውሊድም ታሪክ ሲጠና የተጓዘበት ደረጃ ከዚህ የተለየ አይደለም።

በጎዳና ላይ ኢፍጣር የተደረገው ሰእላ ሰእሎችንና ቅርፃ ቅርፆችን መሰራት፣ እደባባይ ይዞ መውጣትና የቢድአው እጃቢ ማደረግ የሚያሰከትለው ችግር ምንድን ነው? ነገ ከነገ ወዲያ፣ በዚህም ሆነ በሚቀጥለው ትውልድ በሰእላ ሰእሎቹና በቅርፃ ቅርፆቹ ምን እንደሚሰራ ወይም ወደ ምን አይነት ሌላ ቢድአ ሊሸጋገር እንደሚችሉ አሁን መተንበይ አይቻልም። ሆኖም ለሸሪአዊ አምልኮ በተጨባጭ የሰጋት ምንጭ የመሆናቸው ጉዳይ ግን አጠያያቂ አይደለም።

የኑህ ህዝቦች ሽርክ የጀመሩበትን ቢድአዊ ኢባዳ ማሰታወሰ በቂ ነው። መልካም አሰበውና አሏህን ለመገዛት ብለው የጀመሩት ቅርፃ ቅርፅ፣ መዳረሻው የለየለት ሽርክና በመጨረሻም ውህ መሰጠም ነው የሆነው። የካእባን ምሰል ያቆሙት የአላባዎቹ ሙሰሊሞች ወይም ከእነሱ የኮረጁ የሌላ አካባቢ ሙሰሊሞች ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ሀሳዊውን ካእባ መጥወፍ ሊጀምሩ የማይችሉበት መንገድ ዝግ አይደለም። ያኔ ማለቃቀሱ ግን ጥቅም አይኖረውም - ቢድአ እግሩን ከተከለ በኋላ ለመንቀል የሚደረገው ትግል ማገዶ ጨራሽ ነው። ያም ሆኖ ላይሳካም ይችላል።

ሲጠቃለለ፦

ይህንን "የጎዳና ላይ ኢፍጣር" የሚባል አዲሰ መጤ ቢድአ ሰሙንና ግብሩን፣ በማንቆለጳጰሰና የኢሰላምን ካባ በማልበሰ በደምቀት እያሰከወኑትና ቀጣይ እንዲሆን ለማድረግ እየጣሩ ያሉት እካለት ዋናዎቹ ሶሰት ናቸው - የጎዳና ላይ የኢፍጣር ዝግጅትና ክንውን በመኖሩ ያላቸውን ግለዊ ዝናና ታዋቂነት ለማሰጠበቅ የሚሰሩ፣ የንግድ ገቢያቸውን የሚያሳልጡና የሰልጣን ወንበራቸውን ይበልጥ ለማጠናከር የሚፈልጉ እካለት።

"ሸሪአዊ ነው" ካሉ ማሰረጃቸውን ማቅረብ አለባቸው፤ ሀያሉ አሏህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፦

"ከሃይማኖት አሏህ በእርሱ ያልፈቀደውን ለእነርሱ የደነገጉ ተጋሪዎች ለእነርሱ አልሏቸውን?" (አል-ሹራ፣ 21)

መሰሊሙ ህብረተሰብ በባነርና በዲኮሬሽን ድምቀት፣ በመግለጫ ጋጋታና በተሳታፊ ቁጥር ብዛት የጎዳና ላይ ኢፍጣርን ለማሰዋብና ለማሰቆነጃጀት በሚደረገው ድራማ ሳይሸወድ፣ "የጎዳና ላይ ኢፍጣር ሸሪአዊ ከሆነ የቁርእንና የሀዲሰ ማሰረጃው ምንድነው? ሸሪአዊ ከሆነ ካለፉት ዘመናት ጀምሮ እሰካሁን ድረሰ ለምን አልተከናወነም?" በማለት ሊጠይቅና ከዚህ አዲሰ መጤ የእምልኮ ተግባር ሊርቅ ይገባል - ልብ ያለው ልብ ይበል!

በዶ/ር ጀማል ሙሐመድ

ከባህር ዳር እህለሱና መሻይኾች ገፅ ተወሰዶ በAbu Imran ተዘጋጀ